ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2016/12

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በጅጅጋ የተከፈተው የእርድ አገልግሎት መስጫ አርብቶ አደሮችን ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር እንደሚያገናኝ ተጠቆመ

ጅጅጋ፣ኢትዮጵያ፣ የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም፡- ይህ በአሜሪካ መንግሥት መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ መርሀ ግብር ባደረገው ድጋፍ የተከፈተው የእርድ አገልግሎት መስጫ፤ በኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች ትልቁና አስተማማኝ የሆነ ሲሆን፤ ሥራ በጀመረበት በመጀመሪያው ዓመት ብቻ 55,000 አባወራዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የእንስሳት ሽያጭ ያከናውናል ተብሎ ይጠበቃል።

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ(USAID) የገበያ ዕድሎችን በማስፋፋት የአርብቶ አደሩን አቅም መገንባት የተሰኘ መርሀ ግብር ለእርድ አገልግሎት ሰጭው ድርጅት ባደረገው የ 1.5 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የአግልግሎት መስጫው ሊቋቋም ችሏል። ይህ ገንዘብ ድጋፍ የግሉ ዘርፍ ተገቢው አቅም ኖሮት በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የእርድ አገልግሎት መስጫና ማደለቢያ እንዲገነባ አስችሏል። ይኸው አገልግሎት መስጫ በኢትዮጵያ ትልቁ የእርድ እንስሳት መገኛ በሆነውና ከክልሉ ዋና ከተማ ከጅጅጋ 40 ኪ.ሜ. ላይ በሚገኘው የፋፋን መንደር ነው።

አገልግሎት መስጫ ማዕከሉ በዛሬው ዕለት ማለትም የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ፣የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ክቡር አቶ አብዲ መሐሙድኑር ኦማር፣እንዲሁም ከፍተኛ የመንግሥትና የአጋር ድርጅት ኃላፊዎች በተገኙበት ተመርቋል። የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የእርድ አገልግሎት መስጫ እንዲገነባ የተደረገውን ጥረት የደገፈው በዋናነት አካባቢው በኢትዮጵያ ትልቁ የእንስሳት ሀብት ያላቸው አርብቶ አደሮች የሚገኙበት ከመሆኑ አንጻር አርብቶ አደሮቹ ለሚያረቧቸውም ሆነ ለሚያደልቧቸው እንስሳት አስተማማኝ ገበያ እንዲኖራቸው በሚል ነው። ይህም ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ አባወራዎች ገቢ ያድጋል፤አዳዲስ የሥራ ዕድሎች ይፈጠራሉ፤ የአርብቶ አደሮቹም አቅም እየተጠናከረ ይሄዳል።

የእርድ አገልግሎት መስጫው በዓለም አቀፍ የጥራት መስፈርቶችን ሃላል የሆኑ የሥጋ ምርቶችን በማቀነባበር ወደ መካከለኛው ምሥራቅ፣አፍሪካ እና እስያ ይልካል። ይህ የእርድና የማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአንድ የስምንት ሰዓታት ፈረቃ የ200 ከብቶችንና የ2000 ፍየሎችንና በጎችን እርድ የማከናወን አቅም አለው። በተጨማሪም በቀን 15 ሜትሪክ ቶን በሚጥሚጣ የታሸ የበግና የፍየል ሥጋ፤ እንዲሁም 20 ሜትሪክ ቶን በማቀዝቀዣ የተያዘ አጥንት የወጣለት ቀይ ሥጋ ለውጭ ገበያ ያቀርባል።

የማቀነባበሪያ ፋብሪካው ባለቤትና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፋይሰል ጉሃድ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ በተናገሩበት ወቅት፡-“የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ድርጅታችንን ወደ ትልቅ፣ ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማው እና ማኅበረሰቡን የሚያግዝባቸውን በርካታ መንገዶች በመዘርጋት ላይ ያለ የንግድ ድርጅት ስላደረገው ታላቅ ምስጋና ይገባዋል፡፡ ኤጀንሲው ባደረገለት ድጋፍ የገበያ ዕድሎችን በማስፋፋት የአርብቶ አደሩን አቅም መገንባት የተሰኘ መርሀ ግብሩ ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን፤ ከአርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ የእርድ እንስሳት መረከቡን ይቀጥላል” ብለዋል፡፡

አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክም በሰጡት አስተያየት፡-“በሶማሌ ክልል የተቀነባበረ የሥጋ ምርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ፣እስያና በአፍሪካ ውስጥ ወደተለያዩ አካባቢዎች መላክ መጀመሩን ስናስብ ኩራት ይሰማናል፡፡ አሜሪካ የዚህ ሂደትና ስኬት አካል በመሆኗ ኩራት ይሰማታል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የዚህ እርድና የሥጋ ምርት ማቀነባበሪያ የተቋቋመበት የገንዘብ ድጋፍ የተገኘው ከአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ሜርሲ ኮር ከሚያስተዳድረው የፈጠራና የመዋዕለ ንዋይ ፈንድ ሲሆን፤ የፈንዱ ዓላማ የአርብቶ አደር አባወራዎችን ገቢ ማሳደግና አደጋን የመቋቋም አቅማቸውን መገንባት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በየአካባቢው ያለውን ካፒታል በመጠቀም የገበያ ትስስርን በመፍጠር፣ የሥራ ዕድሎችን በማመቻቸት እና ሁሉን-አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ተጠቃሚነትን በመዘርጋት ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የገበያ ልማት እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ ላይ ያተኩራል፡፡

##